በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የጋብቻ ፍቺ


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ሐምሌ ፲፰ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# ጋብቻና ፍቺ

- “እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።” በማለት ሰው በፈትነት ለብቻው መኖር የማይገባው መሆኑን ገልጦልናል። ዘፍጥ 2፡18።

- በአዳምን በሔዋን በደል ምክንያት የተበደለውንም ጋብቻ አምላካችን በመዋዕለ ሥጋዌው የመጀመሪያውን ተአምር ለጋብቻ በማድረግ ጋብቻን ወደ ነበረበት ክብሩ መልሶታል። *ዮሐ 2፡1-11።* በዚህም ጌታችን ጋብቻን የሰው የተቀደሰ ሕይወት አድርጎ ባርኮታል። የውሃውም ወደ ወይን መለወጥ በምድር በምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን በሚፈጸመው የጋብቻ ምስጢር ተጋቢዎቹ ከተራ ሰውነት መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸውና በምድር ሆነው ሰማያዊ ሕይወት የሚመሩ ወደ መሆን የሚለውጣቸው መሆኑን የሚተረጉም ነው።

- በጋብቻው ለሚኖሩ ባልና ሚስትም ጋብቻቸውን የሚመሩበት ሕግና መመሪያ “ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ .... ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ” በማለት ሰጥቷል። ኤፌ 5፡22-29። ይህን የመሰሉ የጋብቻ ሕጎች ሲጣሱ ግን ጋብቻው ይፈርሳል።

- በክርስትና ትምህርት ጋብቻ ሊፈርስ የሚችለው በዝሙት ምክንያትነት ብቻ ነው። “እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።” እንዳለው። *ማቴ 19፡9፤ ዘሌዋ 18፡8-21፤ ዘኍ 5፡12፤ ዘዳግ 5፡21፤ ዘዳግ 22፡13-29፤ ሚል 2፡1-17።*

# ትዳርን የሚጎዱት ምንድር ናቸው?

*ዛሬ ለሚታዩት ከፍተኛ የጋብቻ ፍቺዎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ምንድር ናቸው?*

- ከአቅም በላይ በሆኑ ሆኔታዎች መወጠርና የሰውነት መዛል ወይም መድከም
    - በተለይ ሞያዊ እውቀታቸውን ለማስፋት ትምህርት ቤት የሚገቡ ወጣቶችንም ጭምር የሚመለከት በዚህ ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን።
    - በአንድ ወቅት ኮሌጅ መግባት፤ በመደበኛና በትርፍ ሰዓቶች መሥራት፤ ልጅ ወልዶ ማሳደግ፤ ቤት መሥራት ወይም መግዛት፤ ንግድ መጀመርን በጠቅላላው በአንድ ጊዜ ለማከናወን መሞከር የለብንም።

- ከአቅም በላይ በዕዳ ወይም በብድር መወጠርና ገንዘባችንንም እንዴ መጠቀም እንዳለብን ባለመስማማት የተነሳ የሚፈጠሩ ግጭቶች።

- ራስ ወዳድነት፡- የዓለማችን ሰዎች ሁለት ዓይነት ናቸው። እነርሱም ሰጪና ተቀባይ ይባላሉ። በሁለት ሰጪዎች መካከል የሚኖር ጋብቻ መልካም ወይም ውብ ነው። በሰጪና በተቀባይ መካከል ግን ግጭቶች መኖራቸው የማይቀር ነው።
    - ሁለቱም ተቀባዮች ከሆኑ በተወሰኑ ሳምንታት ውስጥ ይለያያሉ።
    - ራስ ወዳድነት ትዳርን ፈጽሞ የሚያስጠላ፤ የሚሰለቸና ተጋቢዎቹም ሊኖሩበት የማይፈልጉት እንዲሆን ያደርጋል።

- ከጋብቻ ዘመዶች ጋር የሚኖር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት

- ሊጨበጥ የማይችል ግምት፤ አንዱ ሌላውን ፋታ መንሳቱ፤ ሌላ መመኘት (መፈለግ)

- የሴቶች ለመውለድ አለመቻልና የረጅም ዓመታት ሕመም

# ዛሬ ለሚታዩት ከፍተኛ የጋብቻ ፍቺዎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ምንድር ናቸው?

- የገቢ ምንጮች መቋረጥ፣ የንግድ ተቋሞች መክሰር…
- በንግድ ውጤታማ ወይም ስኬታማ መሆን
- ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ ጋብቻን መፈጸም
    - ከ14 እስከ 17 ዓመት ባለው ዕድሜ ውስጥ ሆነው የሚያገቡ ልጃገረዶች ለአቅመ ሔዋን ደርሰው ከሚያገቡ ልጃገረዶች በእጥፍ ከፍያለ ፍቺ ያጋጥማቸዋል።
    - የጉርምስና ጊዜ አፍላ ስሜትና ለጋብቻ ዕድሜ ሳይደርሱ ማግባት ከፍተኛ ጫናና ትርምስ በመፍጠር ተጋግዘው በአጭሩ የትዳርን ዕድሜ ይቀጫሉ።
    - አስቀድሞ ጉርምስናን በመጨረስ ወደ ጋብቻ መድረስ ተገቢና ብቸኛ መንገድ ነው
- አልኮል መጠጦችን ማዘውተርና ስካር
- ልቅ የወሲብ ፊልሞችን መመልከት፣ ቁማር፣ እና ሌሎችም ሱሶች
- አደንዛዥ እጾችን (ጫት፣ ሺሻ፣… ) ማዘውተር
- በዓለም ያሉትን ሥጋዊ ወይም መንፈሳዊ ነገሮችን በአግባብ አለማየት።

# <u>የጋብቻ ፍቺ</u>

- <u>*ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ*</u> "አዳም ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የሚገባው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ብዙ ሴቶችን ይፈጥርለት ነበር፤ በሥነ ፍጥረትም ሆነ ሰው እንዲሚመራበት በሰጠው ትእዛዙ ባልና ሚስት ሳይፋቱ እስከ መጨረሻው አብረው እንዲኖሩ አምላካችን እግዚአብሔር አዝዟል" በማለት ተናግሯል፡፡

- ከፈረሰ ትዳር የተገኙ ወጣቶች ትዳራቸውን አጽንተው ከሚኖሩ ወላጆች ጋር አብረው ከሚኖሩ ወጣቶች ይልቅ ለወንጀልና ወንጀለኝነት መበራከት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

- ፍቺ ከጋብቻ በፊት ለሚፈጸም የእርስ በርስ መተዋወቅና ያለ አግባብም ለሚወለዱ ልጆች ምንጭ ነው፡፡ በተጨማሪነትም ፍቺ ለድህነት፤ ለአካላዊ ጤንነት መጓደል፤ ለአእምሮ መታወክ፤ ጾታን ዕድሜን እና የገቢን ሁኔታም ከቁጥር ውስጥ ሳያስገባ ለሚከሰተው የአደንዛዥ እጾች ሱሰኝነትም ያጋልጣል፡፡

# ትዳርን ከፍቺ ለመጠበቅ ምን እናድርግ?

- "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።" *መዝ 127፡1።* እንደተባለው ፍጹም ደስታና የምንሻው በሕይወታችን ሊነግስ የሚችለው እግዚአብሔር በትዳራችን፤ በቤታችን፤ በምናደርገው ነገር ሁሉ መካከል ካደረግነው ብቻ ነውና እግዚአብሔር የትዳሩ መሪ መሆኑ ዘወትር የተጠበቀ እንዲሆን እናድርግ። ባልና ሚስት አብረው ይጸልዩ፤ መጽሐፍ ቅዱስንም አብረው ያንብቡ። ።

- *በቆላስዩስ 3፡12-14።* "እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ። እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቀፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ። በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት።" በማለት እንደተጻፈው ራሳችንን በነዚህ የቅድስና መመሪያዎች የገዛን እንሁን።

- የትዳር አጋራችንን ቅዱስ ጳውሎስ በገለጣቸው በነዚህ በጎ ጎዳናዎች ለመውደድ የበቃን የሚያደርገን እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ እንወቅ። 1ኛ ቆሮ 7፡27፤

- "እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል።" *ሚል 2፡15* እንደተባለው ትዳራችንን ከማታለል የጸዳ እናድርገው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።